# ፍትሃዊና ነጻ ምርጫ

ፍትሃዊና ነጻ ምርጫ ይሚሉት ሶስት ቃላቶች በውስጣቸው የያዙትን ጽንሰ ሃሳብ፣ ከተባበሩት መንግስታት የሰባዊ መብቶች ድንጋጌ ጋር የተያያዙ ስልሆነ፣ በመጀመሪያ ማየት ያስፈልጋል።

## 1. ሰባዊ መብትና ነጻ ምርጫ

በፈረንጆች አቆጣተር፣ በ1948 የተባበሩ መንግስታት የተስማሙበት የሰባዊ መብት ድንጋጌ፣ የሁለተኛው አለም ጦርነት ያስከተለውን የሰው ልጆች ስቃይ ሁለተኛ እንዳይደገምና በህግ ለመገዛት የተስማሙበት ሰነድ ነው። እንድሚታወቀው በሁለተኛው አለም ጦርነት ጊዜ ከ 60 ሚሊዮን ህዝብ ሞቶአል። ንብረት ወድመዋል። ዜጎች ተርበዋል፣ ተሰደዋል። ከተሞች ወድመዋል። ስለዚህ እንደዚህ አይነቱ ስቃይ እንዳይደገም፣ የሰው ልጆች ሰባዊ መብት እንዲከበር፣ ሰላም እንዲሰፍን :

"ማንኛውም ሰው በዘር ፣ በቀለም ፣ በፆታ ፣ በቋንቋ ፣ በሃይማኖት ፣ በፖለቲካ ወይም ሌላ አመለካተት፣ በብሄረሰብ ወይም ምህበራዊ ምንጭ፣ በንብረት፣ በትውልድ ወይም በሌላ ሁኔታ ምክንያት ልዩነት ሳይደረግበት በዚህ መግለጫ ውስጥ የተደነገጉት መብቶችና ነጻንቶች ሁሉ ተጠቃሚ ነው ይላል። ፣ በመወለድ ወይም በማንም ላይ ሳይለይ ሁሉንም መብቶችና ነፃነቶች የማግኘት መብት እንዳለው ይገልጻል፡፡"

በሌላ በኩል ፣ የ1948 የተባበሩት መንግስታት የሰባዊ መብቶች ድንጋጌ አንቀጽ 21 ፣ የመንግስት ስልጣን መሰረት የህዝብ ፍላጎት መሆኑን እውቅና በመሰጠት ፣

> *"ማንኛውም ሰው ብቀጥታ ወይም በነጻ በተመረጡ ተዘካዮቹ አማክኝነት በሀገሩ የመንግስት አስተዳደር የመካፈል መብት አለው ይላል። በተጨማሪም የህዝብ ፍላጎት የመንግስት ስልጣን መሰረት ይሆናል።ይህ ፍላጎት በሚስጥር ድምጽ በመስጠት፣ሂሉም በእኩልነት በሚሳተፍባቸውና በየወቅቱ መሚደረጉ ምርጫዎችና ድምጽ በነጻ በሚሰጥባቸው ስነ ስራቶች ይገለጻል ይላል።"*

በአንድ አገር አንድ ዜጋ ኑሮውን በሚመለከት ለሚያነሳቸው ጥያቄዎችም ሆነ አስተዳደራዊ ጉዳዮች በሚመለከት ከመንግስት መልስ ለማግኘት የሚያበቃው አንዱ መንገድ፣ በምርጫ ጊዜ ድምጽ መስጠት ሲችል ነው። ስለዚህ የድምጽ መሰጠት መብቱ ሊከበርለት ይገባል።

## 2. የምርጫ ፍትሃዊነት

ሌላው ይምርጫ ጽንሰ ሃሳብ የምርጫ ፍትሃዊንውት ነው። መመዘኛውም፣ አንደኛ የምርጫው ሂደት ግልጽ (transparant); ሁለተኛ ሁሉን ያካተተ (inclusive)ና፣ ሶስተኛ ተጠያቂነት የሚሉት ሲሆኑ(accountability)፣ የምርጫ ተወዳዳሪዎች ለሚአደርጉት እንቅስቃሴ እኩል እድል መስጠን ይጨምራል።

ምርጫ ሁል ጊዜ ፍትሃዊ አልነበረም። ለምሳሌ የሴቶች የመምረጥም ሆነ የመመረጥ መበት ባልተከበረበት ዘመን፣ ምርጫ ፍትህዊ ነበር ማለት አይቻልም። እዚህ ላይ፣ ለሴቶች መብት የታገሉትን የእንግሊዝ ሴቶችን ማንሳት እወዳለሁ። እንግሊዝ አገር; ለወንዶች የመምረጥና የመመረጥ ሙሉ መብት ሲሰጥ፣ የህበተሰቡ ግማሽ አካል ልሆኑት ሴቶች ግን መብታቸውን ነፍጎ ለብዙ አመታት ቆይቶአል። ሴቶች እራሳቸውን አደራጅተው ባደረጉት ትግል በ1918 የመጀመሪያውን ውስን ድል አገኙ። ሲቶች በህብረተሰቡ ውስጥ ባላቸው ሃብትና ቦታ 30አመት ከሞላቸው ሆነ መመረጥ መምረጥ እንደሚችሉ ተደነገገ። ለወንዶች ግን የእድሜ ገደቡ 21 አመት ነው። ተግላቸውንም በመቀጠል በ1928 ሙሉ ድምጽ የመስጠት መብታቸውን ተጎናጽፈዋል። ፈረንሳይ አገር ይህ መብት የተገኘው 1944። በቤልጂግ ይሄ መብት የተገኘው በ 1949 ነው።

ፍትሃዊና ነጻ ምርጫ ለማካሄድ፣ የ1948ቱ የተባበሩት መንግስታት የሰባዊ መብቶች ድንጋጌ ትልቅ ቦታ አለው። ***እውቅና የሰጠው የግልሰቦች መብት አለምንም መሰናከል፣ በመንግስት፣በተወዳድሪዎች፣ ጉዳዩ በሚመለከታቸው የአስተዳደር ሃላፊዎች፣ ሙሉ በሙሉ መከበር እንደአለባቸው ያሰገነዝባል። ሰባዊ መብቶች፣ የሰው ዘር የማይገሰሱ ተፈጥሮአዊ መብቶች በመሆኑ፣ ማንም ዜጋ በዘር፣ ብጾታ፣ በሃይማኖት፣ በቀለም፣በፖለቲካ፥በብሄረሰብ ወይም ማህበራዊ ምንጭ፣በንብረት፣ በትውልድ ምንም አይነት ልዩነት ሳይደረግበት የሰባዊ መብቶችና ተጠቃሚ ነለመሆኑ መሰረት የጣለ ድንጋጌ ነው።***

እነዚህ መብቶች ሁሉም እርስ በርሳቸው የተያያዙ ፣ እርስ በርሳቸው የሚደጋገፉ እና የማይነጣጠሉ ናቸው ። መርሆዎቹ–ሁለንተናዊ (universal )እና የማይነጣጠሉ (interdepedent)፣ የማይከፋፈሉና(indivisible) ተሳሰሩና እና የማይነጣጠሉ ናቸው።

እነዚህን የሰው ልጆች የማይገሰሱ መብቶች በተግባር ለመተርጎም፣ ዲሞክራሲያዊ ተቅዋማት ያስፈልጋሉ። ዲሞክራሲ ስራትና ሰባዊ መብቶች እርስ በራሳቸ የተሳሰሩ ናቸው። ስባዊ መብት ያለዲሞካርሲ ስራት፣ ዲሞክራሲ ያለሰባዊ መበት መከበር ሊኖር አይችሉም።

## 3. የፖለቲካ ፓርቲዎች ሚናና ሃላፊነት

የፖለቲካ ፓርቲዎች፣ አንድ አይነት ርእዮተ አለም ያላቸው ወይም ተመሳሳይ የፖለቲካ አቋዋም ያላቸው የግለሰቦች ስብስብ ሲሆን፣ በምርጫ ጊዜ የየፓርቲያቸውን አማራጭ አጀንዳቸውን ተግባራዊ ለማድረግ እጩዎቻቸውን አቅርበው ፓርላማ ለመግባት የሚዘጋጁበት ወቅት ። በዚህም ምክንያት የዲሞክራሲ ስራት አንድ አካል ናቸው ማለት ይቻላል።

የፖለቲካ ፓርቲዎች ከዚህ በላይ የተጠቀሱትን የተባበሩት መንግስታት ሰባዊ ድንጋጌዎች ማክበር፣ በድርጊት መተርጎም፣ የቀን ተቀን እንቅስቃሴያቸው ሁሉ መመሪያ ማደረግ ግዴታቸው ነው።

የፖለቲካ ፓርቲዎች፣ ዋና አላማና ግብም ፣ ምረጡኝ ለሚሉት ህዝብ፣ በተለይም በአለም አቀፉ የኢኮኖሚ፣ የማህበራዊና ባህላዊ መብቶች ድንጋጌ መሰረት የህዝቡን ኑሮ ለማሻሻል፣ ለችግራቸው መፍትሄ ይሆናል የሚሉትን ፖሊሲ በይፋ ለውይይት ማቅረብ ይጠበቅባቸዋል። እነዚህም

መብቶች፣ ለአንድ ዜጋ በክበርና በነጻነት ለህልውናው የሚስፈልጉትን መሰረታዊ  የሆኑትን እንድ በቂ ምግብና ውሃ ማግኘት፣ መኖሪያ ቤት፣ የጤና ግልጋሎትና ትምህርት የሚስፋፋበትን፣  የስራ መስክ የሚዳብርበትንና የመሳሰሉትን የልማት ጥይቄዎች ቢመረጡ እንዴት ስራ ላይ እንድሚያውሉት ማስረዳት ይኖርባቸዋል። በአጭሩ  የፖለቲካ ፓርቲዎች ለመራጭ አማራጭ ይዘው መቅረብ ይጠበቅባቸዋል።

## 4. የምርጫ ስነ ምግባር Code of conduct

በምርጫ ጊዜ የፖለቲካ ፓርቲዎችም ሆኑ መንግስት እንዲሁም ምርጫው የሚመለከታችው የአስተዳደር ክፍሎች፣  በተለይም እንደእኛ ያለ በሽግግር ላይ ያለ  አገር ፣ ሊያከብራቸው የሚገባ  የምርጫ ስነ ምግባሮች አሉ።  ከነዚህም ዋናዋናዎቹ  በምርጫ ቅስቀሳ ጊዜ

- አንዱ ፓርቲ የሌላውን ፓርቲ መብት፣ ማለትም በነጻ ፕሮግራሙን የማሰራጨት፣ ሃስቡን ያለፍርሃት ከቦታ ቦታ በመዘዋወር ለህዝብ የማስተዋወቅ መብቱን ማክበር፣
- መራጮች በፈለጉት መንገድ፣ በፈለጉበት ቦታ በምርጫው  ሂደት ውስጥ የመሳተፍና ለሚፈልጉት ፓርቲ ድጋፍ የመስጠት መብታቸውን ማክበር፣
- አንዱ የሌላውን ፓርቲ የቅስቀሳ ሂደት አለማደናቀፍ፣ የተቀናቃኝ ፓርቲ እጩዎች ከማዋከብና ከማስፈራራት መቆጠብ፣
- ዓመፅንና  ማስፈራራትን  ካዘሉ ድርጊቶች መቆጠብ፣ የጥላቻ አነጋገርን ማንም ይፈጽምው ማን በይፋ  ማውገዝ፣
- አንዱ ፓርቲ የሌላው ፖለቲካ  ፓርቲ  ላይ  የሐሰት  ፣  የስም  ማጥፋት  ወይም የብጥብጥ  ውንጀላዎችን  ከማካሄድ መራቅ፣
- ባልስልጣናት ስልጣናቸውን ተጠቅመው፣ በመራጩ ላይ አላግባብ ትጸኖ አለማድረግ፣
- ከምርጫ  እንቅስቃሴ  ጋር  በተያያዘ  በዘር  ፣  በፆታ  ፣  በጎሳ  ወይም  በሃይማኖት ልዩነት አለማድረግ፣
- የሴቶችን  የፖለቲካ  ተሳትፎ ማመቻቸት፣

## 5. የምርጫ ታዛቢዎች

ታዛቢዎች የምርጫው ጣቢያ ከተለፈተበት ሰአት ጀምሮ፣ ድምጽ ተቆጥሮ፣ ውጤቱ ተፈርሞ ወደሚመለከተው ክፍል እስከሚሄድበት ጊዜ  ድርስ ያለውን አጠቃላይ ሂደት የሚመዘግቡ ናቸው። የድምጽ  አሰጣጥ ሚስጥራዊነት፣ በምርጫ ጣቢያ ያሉ ሁኔታዎች፣ የፓርቲ ተወካዮች መኖር አለምኖራቸው የመሳሰሉትን ይጭምራል።

ከምርጫ በሁዋላ፣ የድምጽ ቆጠራው ሂደት ፍትሃዊ፣ ተአሚነትና ግልጽነት ያለው መሆኑን ለማረጋገጥ፣ የምርጫ ታዛቢዎች ቁልፍ ሚና አላቸው። ምርጫውን በሃላፊነት የሚያስተናግደው እንደ ምርጫ ቦርድ ያለው ትቁዋም፣ ታዛቢዎችን በሚመለከት ግልጽ የሆነ፣ ተወዳዳሪዎቹም የተስማሙበት፣ ስራት ማውጣት ይጠበቅበታል።

ታዛቢዎች እንደ የሁኔታው የፓርቲና የእጩዎች ተወካዮች፣ ገለልተኛ የሲቪክ ድርጅቶች ተወካዮች፣ አለም አቀፍ ድርጅቶች ሊሆኑ ይችላሉ

**መደምደሚያ**

ምርጫና የመድብለ ፓርቲ እንደ ፖልቲካ ስራት በአፍሪካ ውስጥ በስፋት የጀመረው በፈርንጅ አቆጣጠር በ1990 ዎቹ ላይ ነው። እንድ ምታስታውሱት በዚያን ወቅት፣ የበርሊን ግንብ ትንዶ፣ የሶቭየት ህብረት የፈራረሰበት ጊዜ ነበር። የአፍሪካና የምእራብ አገር ግንኙነቶች፣ በሰባዊ መብት መከበር ጥያቄ ላይ የተመሰረተም አልነበረም። ነገር ግን፣ አለም አቀፉ ሁኔታ ስለ ተቀየረ የምራብ አገሮች እርዳትን ከሰባአዊ መብት መከበርና ከምርጫ ጥያቄ ጋር እያያዙት መጡ።

የአፍሪካ አገሮች መንግስታትም ሆኑ በአብዛኛው ተቃዋሚ ፓርቲ፣ ምርጫን የሃገራቸውን ህዝብ መሰረታዊ መብት ለማክመርና ችግሮችን በዲሞክራሲ ለመፍታት፣ የልማት ስራ ላማካሄድ የውጠኑት አይደለም። ምርጫ በአብዛኛው የሚዘጋጀው እርዳታ ለሚሰጡ የውጭ አገር መንግስታት ነው ቢባል ከእውነት አይርቅም። ስለዚህ መንግስትም ሆነ ተቃዋሚ ፓርቲ ምርጫን ለሰባዊ መብት መከበር፣ ለዲሞክራሲ ስራት መዳበር፣ ሃገርን ላማልማት መስራት ይኖርባቸዋል። ቅንድ የፖለቲካ ፓርቲ ምርጫ ካሸነፈ በፓርላማ ውስጥ፣ ከትሸነፈ ደግሞ ከህዝቡ ጋር በመሆን የተለያየ አምራጮችን እያቅረበ መስራት ይኖርበታል።

**ጽጌረዳ ዋለልኝ**

**March 2013**